# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
# Commercial Bank of Ethiopia
## ጋዜጣዊ መግለጫ

### የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን የ2022/23 (እ.አ.አ.) በጀት ዓመት 2ኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም አስመልክቶ የተዘጋጀ

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባለፉት ከ80 በላይ ዓመታት የሀገሪቱን የልማት ፕሮጀክቶችና አጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በፋይናንስ በመደገፍ፣ የባንክ አገልግሎት ተደራሽነትን በመላ ሀገሪቱ በማስፋፋት እና በቴክኖሎጂ የተደገፉ የባንክ አገልግሎቶችን በማስተዋወቅ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና ሲጫወት ቆይቷል፡፡ የሀገሪቱን ፈጣን ልማት ተከትሎ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ የሚካሄዱ የልማት ፕሮጀክቶች ቁጥር እና ግዝፈት በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ በመምጣቱ፣ ባንኩ ይህንኑ የሚመጥን ምላሽ በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በተለይ የኢትዮጵያን የፋይናንስ ዘርፍ የወደፊት ዕጣ ፈንታ የሚወስን ዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የንግድ ባንክ ለመሆን ያስቀመጠውን ርእይ ለማሳካት ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የባንኩን አጠቃላይ ተልእኮ እንዲያሳካ የተዘጋጀው የረጅም ጊዜ ስትራቴጂክ ዕቅድም እየተተገበረ ይገኛል፡፡ የዚህ ዕቅድ አፈጻጸም በየዓመቱ እና በሩብ ዓመቶች ተከፋፍሎ የሚለካ ሲሆን፣ የ2022/23 በጀት ዓመት 2ኛ ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም በቅርቡ ተገምግሟል፡፡

የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ እና ሥራ አመራር ከ ጥር 16 እስከ ጥር 18 ቀን 2015 ዓ.ም. ድረስ ባንኩ ዋና መ/ቤት ያደረጉት የ2ኛ ሩብ ዓመት ግምገማም ባንኩ ርእዩን ከማሳካት አንጻር በመልካም የአፈጻጸም ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አመላክቷል፡፡ በግምገማው ወቅት የተገለጹ ዋና ዋና አመላካቾችም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 2. ሀብት ማሰባሰብ

### 2.1. ተቀማጭ ገንዘብ ማሰባሰብ

በ2022/23 በጀት ዓመት 2ኛ ሩብ ዓመት ከልዩ ልዩ የባንኩ የተቀማጭ ሒሳብ አገልግሎቶች ብር 88.7 ቢሊዮን ተቀማጭ ማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን፣ የባንኩን አጠቃላይ ተቀማጭ ሒሳብ እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2022 ዓ.ም. ከነበረበት ብር 890.1 ቢሊዮን ወደ ብር 978.8 ቢሊዮን ማድረስ ተችሏል፡፡

### 2.2. ብድር ማስመለስ

በግሉ ዘርፍ እና በመንግሥት ለሚካሄዱ የልማት ፕሮጀክቶች በባንኩ ከቀረበው ብድር ውስጥ በ2ኛው ሩብ ዓመት ብር 55.8 ቢሊዮን የብድር ተመላሽ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

### 2.3. የውጭ ምንዛሬ ግኝት

ባንኩ በ2022/23 2ኛ ሩብ ዓመት ከንውኑ ከተለያዩ ምንጮች 1.7 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በመሰብሰቡ የሩብ ዓመቱን ዕቅድ በ111% ማሳካት ችሏል፡፡

## 3. የብድር ስርጭት

ባንኩ በሩብ ዓመቱ በግሉ ዘርፍ እና በመንግሥት ለሚካሄዱ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች እና የንግድ እንቅስቃሴዎች በአጠቃላይ ብር **63.6** ቢሊዮን ብድር አቅርቧል፡፡ ከዚህ ውስጥ ብር 34.7 ቢሊዮን ለግሉ ዘርፍ የተሰጠ ነው፡፡

## 4. የውጪ ምንዛሬ አቅርቦት

ባንኩ በ2022/23 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ለገቢ ንግድ እና ሌሎች የውጪ ምንዛሬ ለሚያስፈልጋቸው የንግድ እንቅስቃሴዎች 3.9 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማቅረቡ ተችሏል፡፡

## 5. የገቢና ትርፍ አፈጻጸም

በ2022/23 2ኛ ሩብ ዓመት ባንኩ ከተለያዩ ምንጮች ብር 58.7 ቢሊዮን ገቢ ያገኘ ሲሆን፣ ከታክስ በፊት ብር 13 ቢሊዮን ትርፍ አስመዝግቧል፡፡ የትርፍ አፈጻጸሙም ከዕቅድ አንጻር 102.4% ነው፡፡

## 6. ጠቅላላ ሀብትና ካፒታል

በ2ኛው ሩብ ዓመት መጨረሻ የባንኩ ጠቅላላ ሀብት ብር 1.2 ትሪሊዮን የደረሰ ሲሆን፣ ካፒታሉ ወደ ብር ወደ 60 ቢሊዮን አድጓል፡፡

## 7. የባንክ አገልግሎት ተደራሽነት

### 7.1. የቅርንጫፍ ስርጭት፡-

- በ2022/23 2ኛ ሩብ ዓመት 2.2 ሚሊዮን አዲስ ደንበኞች የቁጠባ ሒሳብ የከፈቱ ሲሆን፣ የባንኩ ደንበኞች ብዛትም 38.1 ሚሊዮን ደርሷል፡፡
- የባንኩን የቅርንጫፍ አገልግሎት ለማስፋፋት በተከናወኑ ተግባራት 55 አዳዲስ ቅርንጫፎች የተከፈቱ ሲሆን፣ በዚህ ምክንያት የቅርንጫፎቹ ቁጥር 1,879 ደርሷል፡፡
- ሲቢኢ ኑር (ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት) ብቻ የሚሰጡ ቅርንጫፎች ቁጥርም 130 የደረሰ ሲሆን፣ በ 1,815 የባንኩ ቅርንጫፎችም ለዚህ አገልግሎት የተመደቡ መስኮቶች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

## 7.2. የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎት

ባንኩ ለደንበኞቹ በየቀኑ ለ24 ሰዓት ያልተቋረጠ የባንክ አገልግሎት ለማቅረብ በሚያደርገው ጥረት የዲጂታል እና የካርድ የባንክ አገልግሎቶችን እያስፋፋ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት በ2022/23 2ኛ ሩብ ዓመት፡-

- 2.32 ሚሊዮን የካርድ ተጠቃሚዎች በመመልመል የባንኩን የካርድ ተጠቃሚዎች ቁጥር 8.8 ሚሊዮን ማድረስ ተችሏል፣
- 3.3 ሚሊዮን የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት እና 17,145 የኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን በመመልመል አገልግሎቶቹን ተጠቃሚዎች ቁጥር በቅደም ተከተል 6 ሚሊዮን እና 39,865 ማድረስ ተችሏል፣
- የወኪል የባንክ አገልግሎትን ከማስፋፋት አንጻር፣ በግማሽ አመቱ 16,979 አዳዲስ ወኪሎችን በመመልመል የሲቢኢ ብር ወኪሎችን ቁጥር ወደ 36,507ማሳደግ ተችሏል፣
- 99 አዳዲስ የኤቲኤም ማሽኖች የተተከሉ ሲሆን፣ የባንኩ የኤቲኤም ቁጥር 3,120 እንዲሁም የባንኩ የፖስ መክፈያ ማሽኖች 4,734 ደርሰዋል፣
- በባንኩ የዲጂታል አማራጮች አማካይነት ከብር 1.3 ትሪሊዮን በላይ ክፍያዎች ተፈጽመዋል፡፡ይህም ዲጂታል ሥርዓቱ የጥሬ ገንዘብ አጠቃቀምን በመተካት ከአጠቃላይ ክፍያዎች/ልውውጦች የ39.3 ከመቶ ድርሻ እንዲይዝ አድርጓል።

## 8. ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያስቀመጠውን ርእይ በማሳካት ያለበትን ሃገራዊ ኃላፊነት ለመወጣት በስትራቴጂ የተደገፉ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን፣ ባንኩ ይህን እያደረገ ያለው በታዋቂ ዓለም አቀፍ አማካሪ የተጠና የለውጥ (Transformation) በመተግበር ነው። ይህ የለውጥ ትግበራ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ፣ ባንካችንን በሀገሪቱ ኢኮኖሚ እየተጫወተ የሚገኘውን ወሳኝ ሚና አጠናክሮ እንዲቀጥል እና በመጪው ጊዜ በባንክ ኢንዱስትሪው ውስጥ እንደሚከሠት ለሚጠበቀው ብርቱ ፉክክር ዝግጁ እንደሆን እንደሚያግዘው ይጠበቃል፡፡

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ርእዩን ለማሳካት እንዲሁም የሀገራችንን የፋይናንስ ዘርፍ ለማሳደግና የክፍያ ሥርዓቱን ለማዘመን የሚረዱ የተለያዩ ዕቅዶችና ፕሮጀክቶችን በመንደፍ በሩብ ዓመቱ ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን፣ በዚህ ረገድ የተገኘው ውጤት አበረታች ነበር፡፡

## *የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እውነታዎች (Facts)*

- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እ.ኤ.አ. በ1942 በኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ባለቤትነት የተቋቋመ ባንክ ነው፡፡
- ከ80 ዓመታት ባላይ በአገር ኢኮኖሚና ልማት ጉዳዳች ቀዳሚ አጋር በመሆን የዘለቀ ባንክ ነው፡፡
- **የባንኩ ርእይ፡-** የኢትዮጵያን የፋይናንስ ዘርፍ የወደፊት ዕጣ ፈንታ የሚወስን ዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የንግድ ባንክ መሆን።
- **የባንኩ ተልእኮ፡-** ከፍተኛ ብቃት ያላቸው ባለሙያዎችን እና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በተሻሻለ የፋይናንስ ተደራሽነት የባለድርሻ አካላትን ፍላጐቶች ለማርካት በቁርጠኝነት እንሠራለን፡፡
- **የባንኩ ሠራተኞች ቁጥር፡-** ቋሚ ሠራተኞች 39,101 እንዲሁም ጊዜያዊ ሠራተኞች 30,792 የደረሱ ሲሆን፣ በአጠቃላይ 69, 893 ሠራተኞች አሉት፡፡

*ለሚዲያ መረጃ ፍላጎት*
*አቶ አልሰን አሰፋ - የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር*
*ስልክ፡- +251 111 228 755/ +251 911 20 06 36*
*ኢሜይል፡- AlsenAssefa@cbe.com.et*